# የብዕር ጦርነት

አንሙት ከለንደን

እምነት ነፃነቱ፣

እምነት ነፃነቷ፣

እንደሆነ ሀብቱ፣

እንደሆነ ሀብቷ፣

በደሙ ባጥንቱ፣

በደሟ፣ ባጥንቷ፣

የተገነባው ቅርስ፣

ሀውልቱ፣

ሀውልቷ፣

ዞትር እያሳየ

ዞትር እያሳየች፣ ሞታቸውን ሞቱ፣

ሞታቸውን ሞቷ፣

ፍርሃታቸውን፣ እምቢ ባይነቱ

እምቢ ባይነቷ፣

ማጉላቱ፣

ማጉላቷ፣

በእነሱ ዘንድ ሆኖ፣ ሀጢአቱ፣

ሀጢአቷ፣

በኤሌክቲሪክ ሽቦ፣ በሙቅ ውሃ ዘይት፣

እንዳላሰቃዩት፣

እንዳላሰቃዩዋት፣

በመትረየስ ጥይት፣

እንዳልጨፈጨፉት፣

እንዳልጨፈጨፏት፣

እንዲሆን ያውሬ ‘ራት፣
እንዲትሆን ያውሬ ‘ራት፣
መንገድ እንዳልጣሉት፣
መንገድ እንዳልጣኋት፣
ከገደል፣ ቁልቁለት፣
እንዳልወረወሩት፣
እንዳልወረወሯት፣
እንደፈራሹ አካል፣ ታሪክን ቀብረዋት፣
ዳግመኛ ሊገድሉት፣
ዳግመኛ ሊገድሏት፣
ዛሬም እንደትላንት፣
በዚያ ሠማዕት ላይ
በዚያች ሠማዕት ላይ፣ ጦር ከመዘዙባት፣
አለብህ፣ አለብሽ፣ የታሪክ አደራ፣
ከዱሩ፣ ካፈሩ፣ ጮኾ የሚጣራ፣
በብዕር ውጊያውም፣ ፋኖ ተሰማራ።